የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
የልሳነ ሕግ ጋዜጣ
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
በክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14ኛ ዓመት ቁጥር 79
አሶሳ የካቲት 2001ዓ/ም

ያንዱ ዋጋ 5.75
✉ 293


<u>ማውጫ</u>

**አዋጅ ቁጥር 79/2001ዓ.ም.**
**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት**
**የኢንቨስትመንት አስተዳደርን እንደገና ለመወሰን.**

---

በክልሉ ያለውን እምቅ የኢንቨስትመንት አማራጭን በመጠቀም ባለሃብቶች በግልም ሆነ በጋራ ተደራጅተው ሀብታቸውን በማፍሰስ በትርፋማ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሰማርተው የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያፋጥኑበት ሁኔታ ለማመቻቸት፣

በኢንቨስትመንት አሠራር ሂደት ውስጥ ሲከሰቱ የነበሩ ችግሮችን በመቅረፍ መዋዕለ ነዋያቸውን በክልሉ ለሚያፈሱ ባለሃብቶችን መለየትና ማበረታታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለእነዚህ ልማታዊ ባለሀብቶች ተገቢውን ድጋፍ በመስጠትና ተሳትፎአቸውን በማሳደግ የክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ግልጽና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እንዲመራ አንድ ራስን የቻለ አስፈጻሚ አካል በህግ መመሥረትና ሥልጣንና ተግባሩን በግልጽ መደንገግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49/3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደርን እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 79/2001ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

1. ኢንቨስትመንት ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፡፡
2. ባለሀብት"ማለት በህግ የሚጠየቀውን መመዘኛ አሟልቶ በክልሉ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ባለሀብት ማለት ነው፡፡
3. "ጽ/ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡
4. "ቦርድ" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፡፡
5. "ክልል" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ነው፡፡
6. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

## 3. <u>ስለመቋቋምና ተጠሪነት</u>

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት ከዚህ በኋላ ጽህፈት ቤቱ እየተባለ የሚጠራው ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው

የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

2. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለቦርዱና ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ እና አንቀጽ ላይ ለንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የተሰጠው ሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተላልፏል፡፡
3. በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ እና አንቀጽ ላይ የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤትን ለመከታተልና ለማስተባበር የተሰጠውን ሥልጣን ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መተላለፉን ተከትሎ የቢሮው ስያሜ የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ቢሮ ሆኖ በዚህ አዋጅ ተሰይሟል፡፡
4. <u>ዋና መስሪያ ቤቱ</u>

   ዋና መስሪያ ቤቱ በአሶሳ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በተመረጡ በክልሉም ሆነ ከክልሉ ውጭ በተለያዩ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ሊኖረው ይችላል፡፡
5. <u>ዓላማ</u>

   የጽህፈት ቤቱ ዋና ዓላማ አገራዊና ክልላዊ የኢንቨስትመንት ፖሊስዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና አላማዎችን በመከተል በክልሉ ውስጥ በግልና በጋራ የሚካሄዱ የልማታዊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን በማበረታታትና በመደገፍ ለክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ማበርከት ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት

6. **አደረጃጀት**
   1. የክልሉ የኢንቨስትመንት አስተዳደር የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል

   ሀ/ የኢንቨስትመንት ቦርድ፣

   ለ/ የኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት፣

   ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ በተዋረድ ባሉ የመንግሥት መዋቅር ያሉት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች፣
7. <u>**የኢንቨስትመንት ቦርድ፣**</u>

1. በክልሉ ውስጥ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በበላይነት የሚመራናየዘርፉ እንቅስቃሴዎችን ተቀናጅተው የሚፈፅሙትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ በዘህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡

8. <u>**ስለ ቦርድ አባላት**</u>

   ቦርድ የሚከተሉት ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል እነሱም፡-
   1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም የሚወክለው ሰው ሰብሳቢ
   2. የክልሉ ንግድ ኢትዱስትሪ ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አባል

3. ገቢዎች ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አባል
4. የርዕሰ መስተዳድር የዘርፉ አማካሪ አባልና ድምጽ አልባ
5. ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ኃላፊ አባል
6. አካባቢ ጥበቃና የመሬት አስተዳደርና አጠባበቅ ባለሥልጣን አባል
7. ኢንቨስትማንት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አባልና ፀሐፊ
8. ሥራና ከተማ ልማጽ ቢሮ ኃላፊ አባል
9. ውሃ ማዕድን ኢነርጂ ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አባል

9. **ስለቦርዱ ስብሰባዎች**

1. ቦርድ በ15 ቀን አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በስብሰባው ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የቦርዱ ውሣኔዎች በአብላጫ ድምጽ የሚተላለፍ ሲሆን ድምጽ እኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱ የስብሰባ እና አሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

10. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. የክልሉን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣
2. ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የተዘጋጁትን ፖሊስና እስትራቴጂ ተመልክቶ ለክልሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
3. ይህን አዋጅና መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚረይ እና ኢንቨስትመራትን በሚመለከት የተለያዩ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡
4. ለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን በማስመልከት እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያዎችና አዳዲስ ማበረታዎችን በማዘጋጀት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
5. ኢንቨስትመንትን በሚመለከት በጽ/ቤቱ ተወስኖ በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ድርሻ ባላቸው አካላት የሚቀርቡ ይግባኞች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፡፡ በኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ ቦርዱ የሚያስተላልፈው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. የገጠርና የከተማ ኢንቨስትመንት መሬት በሚመለከተው አካል አማካኝነት በቅድሚያ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

7. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላላቸውና ማናቸውም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሬት ይሰጣል፣ ያስተዳድራል ዝርዝሩ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
8. በክልሉ በማዕድን ማምረት ሥራዎች በሚደረግ ኢንቨስትመንት ላይ ይወሰናል፡፡

11. <u>የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

የክልሉ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ስለ ኢንቨስትመንት የወጡ ፖሊስዎች እና ህጐች በክልሉ ውስጥ በትክክል መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፡ ይቆጣጠራል፣
2. የሚቀርቡትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች መርምሮ አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት አዋጆችና ደንቦች ላይ የተደነገጉትን ተፈላጊ ሁኔታዎች አሟልተው ሲገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከዚህም የመነጨውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣
3. በኢንቨስትመንት ህጐች ላይ የሠፈሩ ወይም ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጐጂ የሆኑ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ እንደአስፈላጊነቱ የሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል፣ ጥፋቱን የፈፀሙትን ሰዎች በህግ እንዲጠየቁ ያደርጋል፣
4. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች የሚያቀርቡት የማበረታቻ ጥያቄዎች የህጉን ድንጋጌዎች አሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጦ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፡፡
5. በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እድል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ መረጃዎችን ለባለሀብቶች ያሰራጫል፣ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለእነዚህ ያስተዋውቃል፣
6. ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚረዱ ኤግዚቢሽኖች፣ ስብሰባዎች፣ ሥልጠናዎች፣ ሴሚናሮችና የመሳሰሉትን እንደአግባቡ በክልልና በክልል ውጭ ያካሂዳል፣
7. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አስመልክቶ ተገቢውን የምክርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፣
8. ስለክልሉ በሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አማራጭ እድል የተጠናቀሩ መረጃዎችን እንዲሁም ስለ ክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሪፖርቶችን ለክልሉና አግባብ ላለው የፌዴራል መንግሥት አካላት ያስተላልፋል፣
9. በክልሉ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት በባለሀብቶች፣ በመንግሥታዊ መ/ቤቶችና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እና ትብብር እንዲኖር ያደርጋል፣ ያስተባበራል፣ የቆጣጠራል፣

10. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌዴራሉ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ /ባለሥልጣን/ በኩል ፍቃድ አግኝተው በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ሀገር ባለሀብቶችን የሥራ ተግባራት የከታተላል፣

11. የባለሀብቶች ፎረም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ድጋፍ የሰጣል፣ ይወያያል፣

12. በህጉ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ ስምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣

13. ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

12. **<u>የጽ/ቤት ኃላፊው አሿሿምና ተጠሪነት</u>**

1. ጽህፈት ቤቱ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም አንድ ኃላፊና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፣
2. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለቦርድ ይሆናል፡፡

13. **<u>የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ሥር ለጽህአት ቤቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣
2. ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ሥራውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
3. የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች በክልሉ ሲቪል ሠርቪስ ህግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
4. የጽ/ቤቱን የሥራ ዕቅድና የማስፈጸሚያ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
5. ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
6. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጽ/ቤቱን ይወክላል፡
7. ለሥራው ባስፈለገ መጠን ከሥልጣኑና ተግባራቱ ከፊሉን ለጽ/ቤቱ የበታች የሥራ ኃላፊወችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

14. **<u>የገቢ ምንጭ</u>**

ጽ/ቤቱ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ገቢ ይኖረዋል፡-

1. በክልሉ መንግሥት የሚመደብ በጀት፣
2. ከማናቸውም ሌላ ምንጭ ከሚገኘው ህጋዊ ገቢ፣ እርዳታና ስጦታ፡፡

15. **<u>ስለሂሣብ አያያዝ መዛግብት</u>**

1. ጽ/ቤቱ ትክክለኛና የተሟላ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፣
2. የጽ/ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረትና ሠነዶች በክልሉ ዋና ኦደተር መ/ቤት በየጊዜው ይመረመራል፡፡

16.. **ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻ**

ኢንቨስትመንትን በክልላችን ለማበረታታት ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በተመለከተ የመስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡

17. **ተፈፃሚነት ስለማይኖቸው ህጐች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

18. **መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር 13/1998 ተቋቁሞ የነበረው የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ጽ/ቤት ተላልፏል፡፡

19. **ደንብና መመሪያ ስለማውጣት**

1. የመስተዳድር ም/ቤቱ በዚህ አዋጅ አፈጻጸምና ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. የኢንቨስትመንት ቦርድ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

20. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ የካካቲት 2001 ዓ.ም.

አህመድ ናስር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ኘሬዚዳንት